# የዳበረ ትምህርት ማእከል

## ለ4ኛ እና 5ኛ ክፍሎች



ጥልቅ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ክህሎቶች

አስተማማኝ/እውነተኛ ምርቶች

የ MCPS ስርአተ ትምህርት

MCPS
Rockville, Maryland

ቀደም ሲል ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው ማዕከል በመባል ይታወቅ የነበረ

## የዳበሩ ትምህርቶች ማእከሎች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለዳበሩ-ለበለፀጉ ትምህርቶች ማእከሎችን ያዘጋጃል፣ ቀደም ሲል ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው ማእከል በመባል ይታወቁ የነበሩ ለ4ኛ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች። ማእከሎቹ የታለሙት በፈጣን ሁኔታ ትምህርት የመቀበል ችሎታ ላላቸው እና የላቀ እሳቤዎችንና ረቂቅ፣ውስብስብ/advanced concepts of greater complexity ሁኔታዎችን ለመቋቋም ችሎታ ላላቸው ነው። የፕሮግራሙ ግብ ለከፍተኛ ችሎታና የተነሳሱ የኤሌሜንታሪ ተማሪዎች የተፋጠነና የበለፀገ የትምህርት ፕሮግራም ለማቅረብ ነው። በዚህ ፕሮግራም የሚገቡ ተማሪዎች ልዩ የአካዴሚ መገለጫ እና የትምህርት ፍላጎት ያላቸውና ከመደበኛ የመማሪያ ክፍሎች ይልቅ በነዚህ ማእከሎች በቀላሉ ለማግኘት ለመረዳት ወይም ለማወቅ ይችላሉ። ማእከሎቹ የሚያቀርቡት የትምህርት ዘይቤ የአስተሳሰብ ክህሎት፣ ደፋርነትን፣ እና ፈጠራዊ አገላለጽን በማራመድ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች እምቅ ችሎታቸውን እንዲገነዘቡት ማድረግ ነው።

## ማእከሎቹ የታለሙት ለማነው?

ማዕከሎቹ የታለሙት በአጥቢያ መደበኛ ት/ቤቶቻቸው በችሎታቸው ልክ የሚመጥን ፍላጎታቸውን በቀላሉ ለማግኘት ለማይችሉና ከእኩዮቻቸው ብልጫ ላላቸው ተማሪዎች ነው። ማእከሉ የሚያተኩረው የዳበረ እና የበለጸገ በፍጥነት የሚማሩት የንባብ፣ የቋንቋ ስነጥበብ፣ ሳይንስ እና ማህበራዊ ጥናቶች፣ ከክፍል ደረጃቸው በላይ የሆኑ የትምህርት አቅርቦቶችን በመጠቀም ነው። ፕሮግራሞቹ በአሁን ወቅት በስምንት ክልላዊ ማእከሎች እና በአራት የአካባቢ ማእከሎች ላይ ይገኛሉ።

## ድርጅት

ተማሪዎች በማእከሉ ትምህርት ቤት ሲከታተሉ በሁሉም የ4ኛ እና የ5ኛ ክፍሎች እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። 5ኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች ወደ አካባቢያቸው መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) ተመልሰው ለመካከለኛ ደረጃ (ሚድል ስኩል) ማግኔት ፕሮግራሞች ወይም መካከለኛ ደረጃ (ሚድል ስኩል) ኮንሶርሽየም ሊታሰቡ ይችላሉ።

"ይህ ፕሮግራም አእምሮአችንን የሚከፍትና የሚፈታተነን ይመስለኛል። በዚህ ክፍል፣ የፈጠራ አእምሮ ጨመቃ በየእለቱ ይንቀረቀራል፣ እውነተኛ ጥንካሬአችንን መጠቀም ይኖርብናል።"



## የመግቢያ ሂደት

ለ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች በሙሉ ፎል ላይ ስለ ማእከሎቹ በደብዳቤ ማስታወቂያ ይነገራቸዋል። ስለ አካባቢዎ ት/ቤት ወይም የግል ት/ቤት መረጃ/ኢንፎርሜሽን በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡-www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms. ቤተሰብ ከእንግዲህ ወዲያ ማመልከቻ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም። በጃኑዋሪ፣ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ ግምገማ ከተደረገ በኋላ የመግቢያ ፈተና/ቴስት ለመውሰድ ለሚችሉት/ብቃት ያላቸው ይነገራቸዋል። ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ፌብሩዋሪ ላይ በት/ቤታቸው በሚካሄድ ከክፍል-ደረጃ-ከፍ ያለ ምዘና/ግምገማ ላይ ይሳተፋሉ። በአካባቢያቸው ከሚገኙ ጓደኞቻቸው የበለጠ የትምህርት ፍላጎት የሚያሳዩ ልጆች በማዕከሉ አንድ ቦታ ላይ እንዲገቡ ሊደረግ ይቻላል። ኮሚቴ በመሰብሰብ የሚከተሉትን ውሂቦች/ዳታ ይመረምራል፣የትምህርት/አካደሚክ ብቃት፣ ደረጃ የጠበቀ ፈተናዎች/ቴስቶች፣ የአካባቢ እኩያሞች ቡድን፣ እና ለተፋጠነና የዳበረ ትምህርት ስኬታማነት ያላቸው አቅም። ስፕሪንግ ላይ የተመረጡትን ውጤት ለቤተሰቦች ይገለጽላቸዋል።

## መጓጓዣ/ትራንስፖርት

ወደ ዳበረ ትምህርት ማእከሎች ደርሶ መልስ መጓጓዣ/ትራንስፖርት የትራንስፖርቴሽን ክፍል በሚወስነው ሁኔታ አማካይ በሆኑ ቦታዎች የሚቆም(መደበኛ የ MCPS ት/ቤቶች) ይቀርባል። የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ከተማሪው መኖሪያ ቤት በርካታ ማይሎች ሊርቁ ይችላሉ። ወደ ማእከላዊ ጣቢያዎች ደርሶመልስ ትራንስፖርት የማቅረብ ሃላፊነት የወላጆች ነው። የአውቶቡስ ጉዞዎች ከአካባቢ ት/ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት በፕሮግራምና ጉልህ በሆነ ሁኔታ ይርቃሉ በሰርጭት ስፍራም ይለያያሉ። እባክችሁ የትራንስፖርት አማራጮችና ሀላፊነቶችን በጥሞና አገናዝቡ። ዝርዝሮቹ በምርጫ ጊዜ ከMCPS የትራንስፖርት መምርያ ይገኛሉ።

## አካዴሚያዊ አካባቢ

ማእከሎቹ የMCPSን ሥርዓተ ትምህርት/ካሪኩለም የሚያዳብር፣ የሚያፋጥን፣ እና ቀጣይነት ያለው የትምህርት አካባቢ ይሰጣሉ። የተማሪዎቹን ልዩ ፍላጎት ለማሟላት፣ ማዕከሎቹ የሚከተሉትን የማድረግ እድል ይሰጣሉ፡-

- ሀይለኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም በሚሰጥ የትምህርት አካባቢ መሳተፍ።
- በፕሮብሌም ፈቺና ሂሳው፣ ፈጠራዊ፣ እና ገምጋሚ አስተሳሰብ መሳተፍ።
- በአካዴሚያዊ ውይይት መሳተፍና ለአዳዲስ ሀሳቦች ክፍትነት ማዳበር።
- አዳዲስ ፕሮብሌሞችና አዳዲስ መፍትሄዎች ማግኘት፤ ሀቀኛ ውጤቶች መፍጠር።
- ትልቅ ነፃ ጥናት ማካሄድና ከፍተኛ የምርምር ክሂሎት ማግኘት።

# ለተጨማሪ መረጃ

ስለ መግቢያ ሂደት ጥያቄ ለማቅረብ/የበለጠ ለመረዳት፣ የኮንሰርሽያ ምርጫ እና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎቶች/ Division Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS) በስልክ ቁጥር 240-740-2540 ያግኙ።

ስለ ስርዓተ ትምህርቱ ለመጠየቅ/የበለጠ ለመረዳት፣ የተፋጠነና የዳበረ ትምህርት/Accelerated and Enriched Instruction (AEI)ን በስልክ ቁጥር 240-740-3110 ያግኙ።

ድረ-ገጽ:-
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms

እያንዳንዱ ክልላዊ ማዕከል በግልጽ ከተቀመጡት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምድብ/ክላስተርስ ይወስዳል፣ ማእከሎቹ የሚገኙት በሚከተሉት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው።

ሉሲ ባርንስለይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Lucy Barnsley Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ሪቻርድ ሞንትጎመሪ (Richard Montgomery)፣ ሮክቪል (Rockville)፣ ዊተን (Wheaton)

ሼቪ ሼዝ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Chevy Chase Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ቤተዝዳ-ሼቪ ቼዝ (Bethesda-Chevy Chase)፣ ዋልተር ጆንሰን (Walter Johnson)፣ ዊትማን (Whitman)

ክሊርስፕሪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Clearspring Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ክላርክስበርግ (Clarksburg)፣ ዳማስከስ (Damascus)

ኮልድ ስፕሪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Cold Spring Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ቸርችል፣ ውተን (Churchill, Wootton)

ዶ/ር ቻርልስ ር. ድሪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Dr. Charles R. Drew Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ብሌክ፣ ፔይንት ብራንች፣ ሼርውድ፣ ስፕሪንግብሩክ (Blake, Paint Branch, Sherwood, Springbrook)

ፎክስ ቻፕል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Fox Chapel Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ኖርዝዌስት (Northwest)፣ ፑልስቪል (Poolesville)፣ ኩዊንስ ኦርቻርድ (Quince Orchard)፣ ሴኔካ ቫሊ (Seneca Valley)

ሚል ክሪክ ታወን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Mill Creek Town Elementary School)
ምድብ-አካባቢዎች/ክላስተሮች፡- ጌትስበርግ (Gaithersburg)፣ ኮ/ሎ ዛዶክ ማግሩደር (Col Zadok Magruder)፣ ዋትኪንስ ሚል (Watkins Mill)

ኦክ ቪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Oak View Elementary School)
ኢስት ሲልቨር ስፕሪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (East Silver Spring ES, Flora Singer ES)፣ ፎረስት ኖልስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Forest Knolls ES)፣ ሃይላንድ ቪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Highland View ES)፣ ኦክ ቪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Oak View ES)፣ ሮሊንግ ተሬስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Rolling Terrace ES)፣ ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Sligo Creek ES)፣ ውድሊን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Woodlin ES)

ፓይን ክረስት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Pine Crest Elementary School)
አርኮላ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Arcola ES)፣ ግሌን ሄቨን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Glen Haven ES)፣ ግሌናል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Glenallan ES)፣ ሃይላንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Highland ES)፣ ኬምፕ ሚል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Kemp Mill ES)፣ ኦክላንድ ተሬስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Oakland Terrace ES)፣ ፓይን ክረስት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Pine Crest ES)፣ ሮክ ቪው ኤለመንተሪ ት/ቤት (Rock View ES)

የአካባቢ ጣቢያዎች *
ራቼል ካርሰን፣ ስፓርክ ማሱናጋ፣ ፓይኒ ብራንች፣ እና ስቶንጌት አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (Rachel Carson, Spark Matsunaga, Piney Branch, and Stonegate Elementary Schools)

* የአካባቢያቸው ት/ቤት ማእከል ካለው አካባቢ የሆኑ ተማሪዎች ወደ ክልላዊ ማዕከል ለመሄድ ተቀባይነት አይኖራቸውም።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ የኮንሶርሽያ ን/ክፍል የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ።
Department of Materials Management for the
Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)
ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Department of Communications
0012.19ct • Editorial ፣ Graphics & Publishing Services • 8/18 • NP